# ወጣቶች እና የፀረ-ኤድስ ፕሮግራም

ይህንን ፊልም (ድራማ) ለመሥራት በጠቅላላው ስምንት ሰዎች ያስፈልጋሉ፡፡ በድምሩም 13 ገቢር አለው፡፡

(ቁጥር አንድ ሴት)

የመጀመሪያዋ ሴት - ይህቺ ሴት እድሜዋ ከ20 - 30 ዓመት ሲሆን ስሜታዊ" በመሆን በጠለቀ ሁኔታ ማዘን አንዳንዴም የግልፍተኝነት ገጸ-ባሕሪይ ማሳየት ትችላለች፡፡ የምትጫወተው ሚና በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በመቅረጫው ስቱዲዮ ውስጥ ከእርሷ ከፍ ያለ ትእግሥት ይጠበቃል፡፡

ሁለተኛዋ ሴት - ይህቺ ሴት እድሜዋ ከ20 - 30 ዓመት ነው፡፡ እርሷም የምታመዛዝን፣ የተረጋጋች እና ከመጀመሪያዋ ሴት ይልቅ በሳል ሴት ናት፡፡

(ቁጥር አንድ ወንድ)

የመጀመሪያው ልጅ - ይህ ልጅ እድሜው 15 ዓመት አካባቢ የሆነ ሲሆን ድምፁ እንደ ወጣት ልጅ እንጂ እንደ ትልቅ ሰው አይደለም፡፡

ቁጥር 2 ወንድ ልጅ - ይህም ልጅ እንደ ቁጥር 1 ወንድ ልጅ እድሜው 15 ዓመት አካባቢ የሆነ እና ድምጹ እንደ ወጣት ልጅ እንጂ እንደ ትልቅ ሰው አይደለም፡፡

ቁጥር 1 ሰው -ይህ ሰው ከ45 ዓመት በላይ ነው፡፡ ድምጹም እንደ አዋቂ ሰው ነው፡፡

ቁጥር 2 ሰው - ይህ ሰው እድሜው ከ25 - 30 ዓመት ሲሆን የኮሚክ (የአስቂኝ) ገጸ-ባሕርያትን መጫወት የሚችል የሚያስፈግግ፣ ከእርሱ የማይጠበቅ ንግግር (ከእድሜው ጋር የማይሄድ) ሰውን የሚያስቀይም ንግግር የሚናገር ነው፡፡

ቁጥር 3 ሰው - ይህም ሰው እድሜው ከ25 - 30 ዓመት ሲሆን የጨዋ እና የምክንያታዊ" ሰው ገጸ-ባሕሪይ መጫወት የሚችል ሲሆን አስቸጋሪ ፀባይም ተላብሶ መጫወት ይችላል፡፡

ቁጥር 4 ሰው - ይህ ሰው ዕድሜው ከ35 - 40 የሚሆን ነው፡፡

## ገቢር አንድ

ካድር - በሉ! መልካም የሥራ ቀን፣ እንገናኛለን

ማማዱ - እሺ እንገናኛለን

መምህር - ማማዱ ባዶ ወንበር መኖሩን እንዳልተመለከትክ አወቅሁ

ማማዱ - እውነትህን ነው መምህር እዚህ መቀመጥን እመርጣለሁ

መምህር - አሃ ይህን ቦታ መምረጥህ ምክንያቱ ምንድነው ::

ማማዱ - ምክርህን በመቀበል ነው የማደርገው ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ያልከውን እየፈጸምኩ ነው::

<u>የአንደኛው ተማሪ ድምጽ</u>

- ማድረግ አልነበረብህም ማማዱ!

<u>የማማዱ ድምጽ</u>

- ወላጆቼ በኤድስ ምክንያት ሞተዋል አይደለም:: ስለዚህም ስለ እርሱ ማውራት አልሻም መሄዱ መልካም ነው::

<u>የሁለተኛው ተማሪ ድምጽ</u>

ማማዱ! የምትናገረውን ነገር እያገናዘብክ፡፡

መምህር - ማማዱ! እንደ አንተ አይነት አሳፋሪ ሰው አይቼ አላውቅም ፍፁም የሚያሳፍር ድርጊት ነው::

ማማዱ - ነገር ግን መምህር

መምህር - ፈጽሞ አይደለም! ለክፍል ጓደኞችህ ምንም ዓይነት ክብር አታሳያቸውም ከሁሉም በላይ እኛ እንደተረዳነው ስለ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ በበቂ ሁኔታ ልትማር ያስፈልግሃል:: በጣም በጣም ብዙ

- በኤድስም ይሁን በሌላ ቦካሪ ወላጆቹን በሞት በማጣቱ ምክንያት እያዘነ ነው::
- ስለዚህም ሴት አያቱ ካልወሰዱት በስተቀር ዛሬውኑ ወደ ጎዳና ይወጣል::
- ቦካሪ ለማንም ሰው አደጋ አይደለም በአጠቃላይ በማንም ሰው ላይ አደጋ አልጋረጠም ግልጽ ነው::
- አደጋው የሚኖረው አንተ አሁን እያሳየህ ባለው ሁኔታ ላይ ነው:: ማማዱ
- ለዚህም ነው ነገ ለክፍል ጓደኞችህ ስለ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ ጽሑፍ እንድታዘጋጅ የምጠይቅህ
- ትክክለኛውን ስለ ኤድስ መረጃ የምታገኝበት ማዕከል አድራሻ ይህ ነው (አድራሻውን እያሳየ) አሁን ክፍት ነው መሄድ ትችላለህ::
- በልሂድ፣ ከዚህ በኋላ ሥራህን ጀምር::

- <u>የቦካሪ ትንሽ ወንድም</u>

(ይስቃል)

- <u>የቦካሪ ሴት አያት</u>
  - ቆይ!
  - አልፋ! ቀስ በል ቆየን!
- <u>ላይብረሪያን</u> (የመጽሐፍት ቤት ሠራተኛ)

  ደህና አደራችሁ!
- <u>ማማዱ</u>

  ሄይ! ወዴት ነህ?

ካድር - እንዴ! እዚህ ምን እየሠራህ ነው?

ማማዱ - ኡፍ! ይህን የማይረባ ስለ ኤድስ ጽሑፍ እየፃፍኩ ነው አንተስ?

ካድር - እባክህ አዳምጠኝ.. ኤድስ ማለት በትምህርት ቤት ከተማርከው ነገር በጣም የተሻለ መሆኑን አውቀህ

- ወደ አእምሮህ አስገባው::
- ለመሄድ አስቤአለሁ!

ካድር - በእርግጥ ይህን መማርና ማወቅ ይገባሃል:: ታዳምጠኛለህ? ጉዳዩ አሳሳቢ ነው!

ማማዱ - ስለ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ምን ማወቅ ትፈልጋለህ?

<u>የመጽሐፍት ቤት ሠራተኛ</u> - አዎ! ልረዳህ እችላለሁ!

ማማዱ - (ተንፍሶ) ስለ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ማወቅ እፈልጋለሁ::

<u>የመጽሐፍት ቤት ሠራተኛ</u> -

እርግጥ ነው! ኤድስን የሚያመጡ ቫይረስ በአንድ ሰው ውስጥ እንዳለ ለማወቅ የሚረዳ ዘዴ ነው::

በአጠቃላይ በደም ምርመራ የሚገኝ ነው

ማማዱ - ስለዚህም ለምሳሌ - ራሴን የምጠራጠር ከሆነ ልመረመር እችላለሁ?

<u>የመጽሐፍ ቤት ሠራተኛ</u>

- አዎ ለምሳሌ

ማማዱ - የእኔ የራሴ ወንድም!

<u>መምህር (ቲቸር)</u> - አህ! አሁንም ዘገየህ ማማዱ

ማማዱ - አዎ መምህር! በጣም ይቅርታ! በጓደኛዬ እርዳታ ስለ ኤድስ የሰራነውን አቀርባለሁ፡፡

ቲቸር (መምህር)

ጥሩ! ማነው እሱ

መልካም መቀጠል ትችላላችሁ

ማማዱ - ጥሩ ዜና ልንገርህ፡፡ አንድ ሰው የቫይረሱ ሰለባ ቢሆን ምንም ችግር አያስከትልም በተጨማሪም አንድ ሰው በቫይረሱ ቢያዝ አደጋ አያስከትልም፡፡

ተማሪ ቁጥር 3

- ስለዚህ ጉዳይ አስቀድመን እናውቃለን፡፡

በካሪ - ታውቃለህ! ከቤተሰቦችህ አንዱን ማጣት ግን አሳዛኝ ነው

ማማዱ - እንደገና በዚህ ችግር ላይ ሰዎች ባይቀበሉህ ችግሩን መጋፈጥ ይከብዳል

በካሪ - በቫይረሱ ምክንያት ችግር ከገጠማቸው ቤተሰቦች መካከል እንደ እኔ ቤተሰብ መበረታታትንና ቀረቤታ የማይሻ ማነው?

ማማዱ - እንዲህ ዓይነት ቤተሰቦች ችግርን መጋፈጥ የሚያስችላቸው ብርታት ያስፈልጋቸዋል እናም የገንዘብ ችግር ቢገጥማቸው በእርግጥ መፍትሄ ይፈልጋሉ፡፡

ቦካሪ - በእርግጥ የኤድስ ቫይረስ የሚተላለፍባቸው ሦስት መንገዶች አሉ፡፡ በቫይረሱ ከተያዘች ነፍሰጡር ወደ ጽንሱ

ማማዱ - ልቅ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በመፈፀም

ቦካሪ - በቫይረሱ ያልተያዘ ሰው ከቫይረሱ ጋር ከሚኖረው ሰው ጋር የሚኖር የደም ንክኪ

ማማዱ - አዎ ነገር ግን ራስህን ከቫይረሱ መከላከል አስቸጋሪ አይደለም! የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን ለማስወገድ ዋነኛው መንገድ መታቀብ ነው - ማለትም ግንኙነት ባለማድረግ

ቦካሪ - እጮኛ ካለህና ሁለታችሁም ከቫይረሱ ነፃ ከሆናችሁ የተሻለው ነገር በታማኝነት መቆየት ነው፡፡

ማማዱ - መተላለፊያውን ማስወገድ

ቦካሪ - መታቀብንም ሆነ ታማኝነትን ካልተገበርክ ሁል ጊዜ ኮንዶም አለልህ

ማማዱ - በደም አማካይነት መተላለፉን ለማስወገድ መሣሪያዎችን ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ መጠቀም የለብህም እነዚህም ቆዳን እንደሚበሱ ስለታማ ነገሮች እንደ ምላጭ

መርፌ ሌሎች ስለታማ መሣሪያዎችን ማስወገድ ይኖርብሃል፡፡ ያለበለዚያም በእንፉሎት ኃይል መቀቀል ይኖርባቸዋል፡፡

*******

## ገቢር ሁለት

**የበሽታዎች ጠቅላላ ስብሰባ**

ማማዱ ማኪ ባሕ፣ እድሜ 17፣ ማሊ እና የእርሱ ቡድንን ሃሳብን መሠረት ያደረገ

አቅራቢ (ለካሜራ)

ላለፉት 100 ዓመታት በሽታንና ሕመምን በመዋጋት ብዙ መሻሻሎችና አድርገናል፡፡ ነገር ግን በቅርቡ የተከሰተው አዲስ በሽታ ብዙ ስቃይን አስከትሏል፡፡ ይህም በሽታ ኤድስ ይባላል፡፡

-

- እስከ አሁን ምንም መዳኛም ሆነ ክትባት የለውም ነገር ግን ራሳችንን ለመከላከል በጣም ቀላል እና ውጤት ያለው እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ይህም በተረት የምትሰማው እና አሁን እየነገርኩህ ያለው ነው፡፡ ይህም በማይደረስበት ትንሽ ዓለም፣ ለዓይን በማይታይ በአጉሊ መነጽር ብቻ በሚታይ  እና በበሽታዎች ዓለም የሚገኝ ነው፡፡

(በትረካ የሚቀርብ)

በዚህ በሽታዎች ባሉበት ዓለም ልክ እንደ ሰው ምድርና በሽታዎች በሚኖሩበት ከተማ ወይም መንደር አለ በተለይም በሽታዎች እንዲኖሩ የሚያስችል ጀርም አለ፡፡

(በትረካ የሚቀርብ)

እንደ አባል ጓደኞቼ! ኮንታሚኖል ተብሎ በሚታወቅ መንደር ነው የሚኖረው፡፡ የመንደሩም ኃላፊ ኃይለኛ ከሚባለው የቲቢ ቤተሰብ መካከል ይገኛል፡፡

ቲቢ (ማንባ ነቀርሳ)

- ተመልከት ነጭ የደም ሴል!
- አቅራቢ - በዛ መንደር ብዙ ቤተሰቦች አሉ እነርሱም የልጅነት ልምሻዎች፣ የኩፍኞች፣ የወባዎች፣ የጉበት በሽታዎች እንዲሁም የአባላዘር በሽታዎች ለምሳሌም ቂጥኝና ጨብጥ በእርግጥም የተቅማጥ በሽታዎች ቤተሰብ ይኖራል